Association of Ethiopians in Europe

የኢትዮጵያዉያን ማህበር በአዉሮፓ

www.ethiodiaspora.net

**ለኢትዮጵያውያን የስፖርትና ባህል ፌዴሬሽን በአውሮፓ**
**የስራ አስኪያጅ ኮሚቴ**

**ጉዳዩ: ማብራሪያ ስለመጠየቅ**

ፍራንክፈርት ሐምሌ 1-2016 ዓ/ም - July 8-2024

ውድ ወገኖቻችን

በአውሮፓ ሀገሮች የምንኖር ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን የኢትዮጵያውያን ማህበርን በአውሮፓ ስንመሰረት እና የቃል ኪዳን ሰነድ ስናፀድቅ በኢትዮጵያ ሉአላዊነት፣ በሕዝቦቿ ደህንነት እና በህግ የበላይነት አበክረን እንደምንሰራ ቃል በመግባት ነው።

ኢትዮጵያ እንደ ሃገር እየገጠማት የሚገኘው የመፍረስ አደጋ፣ በህዝቧ በተለይም በአማራው ማህበረሰብ ላይ እየተፈጸመ የሚገኘው ግልጽ የዘር ማጽዳት ዘመቻ ፤መንግስታዊ ሽፋን ተሰጥቶት በተቀናበረ መንገድ ላለፉት 6 ዓመታት የብዙ ወገኖችን ህይወት በአጭር አስቀርቷል። ይህንን አስከፊ ሁኔታ እያየንና እየሰማን ምንም አለማድረግ ከህሊና ተጠያቂነት አናመልጥም። ከዚያም አልፎ ይህን ግፍ ከሚፈጽመው ገዢ ቡድን እና አጋፋሪዎቹ ጋር የሚደረግ ሽርጉድ በህዝብና በታሪክ ፊት ከበዳዩ እኩል ተጠያቂ እንደሚያድርግ ልናሳስብ እንወዳለን።

በውጭ አገር የምንገኝ ኢትዮጵያውያን በስፖርት፣ ባህል፣ እና በኪነጥበብ ዝግጅቶች ለሃገራችን ያለንን ፍቅር እና ማንነታችህንን በማጉላት፣ የሃገራችን ስሟን እና ሰንደቅ ዓላማዋን ከፍ አድርጎ፣ አንድነታችንን እና ህልውናችንን መሰረት አድርጎ የሚደረግ ማንኛውንም ቅን እንቅስቃሴ በበጎ እንደምንመለከት እና እንደ ማህበር አስፈላጊውን ትብብር ከማድረግ ወደ ኋላ እንደማንል እናሳውቃለን።

ይሁን እና ዛሬ ህዝባችን አረመኒያዊ በሆነ መንገድ እየተጨፈጨፈ፣ ከቤትና ከመሬቱ እየተፈናቀለ፣ ካለ ፍትህ በእስር እየማቀቀ፣ በእናት አገሩ ላይ እንደ ሁለተኛ ዜጋ እየተቆጠረ፣ ለስደት እና ለግዞት እየተዳረገ ባለበት ሰዓት ፤ ለዚህ ሁሉ ግፍና በደል የመጀመሪያ ተጠያቂ የሆነው የአብይ መንግስት ቢሆንም፤ ከዚህ ሰርአት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚደረግ መሞዳሞድ የማንታገሰው ቀይ መስመራችን መሆኑን ለማሳወቅ እንፈልጋለን። **ከሁሉም በላይ በኢትዮጵያ ስም** እየማለ፤ አማራው ላይ በ**ድሮን እና ከባድ መሳሪያ የታገዘ ጥቃት በመፈጸም በዙ ንጹሃን ዜጎችን ለሚጨፈጭፍ ስርአት፤በተዘዋዋሪ** እራሱ አማራውን ተባባሪ ለማድረግ የሚደረግ ዝግጅት እንደማንታገስ እና ይህንን እኩይ ሴራ ለማክሸፍ ማናቸውንም ህጋዊ እርምጃ ከመውሰድ እንደማንቆጠብ እናሳውቃለን።

አላማችን ለሁሉም ዜጎቿ የምትሆን ኢትዮጵያን እውን ማድረግ ነው። በመጪው ሃምሌ ወር መጨረሻ ቤልጅየም ጌንት ከተማ ይካሂሄዳል ተብሎ በሚጠበቀው የ2024 ስፖርት እና ባህል ዝግጅት ላይ ከህብረተሰቡ ቅሬታዎችን እና ጥቆማዎች እየደረሱን በመሆኑ፡ ተጨማሪ እርምጃ ከመውሰዳችን በፊት ነገሮችን ማጥራት ስላለብን፤ ከዚህ በታች ለምናቀርብላችሁ ጥያቄዎች ግልጽና ቀጥተኛ መልስ በአስቸኳይ በመስጠት እንድትተባበሩን በአክብሮት እንጠይቃለን ?።

1ኛ/ ይህን ዓመታዊ ስብስብ በገንዘብና በቁሳቁስ፤  የሚሳተፉት ድርጅቶች፣ ግለሰቦች እና ተቋማትን ማንነት እና የተሳተፉበትን የገንዘብ መጠን ?

2ኛ/ በ2023 አምስተርዳም ላይ በተካሄደው ተመሳሳይ ዝግጅት የተገኘው ገቢ የኦዲት ዝርዝር ሪፖርት፤ በተጨማሪም ከዚህ የቤልጅየም ዝግጅት የሚገኘው ገቢ በምን ላይ እነደሚውል ግልጽ እንድታደርጉ እንጠይቃለን።

3ኛ/ ይህ ኢትዮጵያውያን በሚታደሙበት ዝግጅት የሚገኝ ገንዘብ ዛሬ በሀገራቸው ላይ ከቀያቸው ተፈናቅለው በየመንገዱ ለወደቁ ወገኖቻችን  ድጋፍና የታሰበ ነገር ስለመኖሩ ግልጽ እንድታደርጉልን እናሳሰባለን።

4ኛ/ ለኢትዮጵያ ህልውና እና ለአማራው ህዝብ ደህንነት ለቆሙ ተቋማት ድምጽ ማሰሚያ መድረክ ለመስጠት ፍቃደኛ መሆናችሁን።

ከዚህ በላይ ላቀርብናልችሁ ጥያቂዎች ተገቢውን መልስ፤ እስከዚህ ሳምንት መጨረሻ
(15 ጁላይ- July 15-2024) ድረስ በጽሁፍ እንድታሳውቁን ስንጠይቅ እኛም እነኝህ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ እስኪያገኙ ድረስ የምንደርስበትን ውሳኔ የምናዘገይ መሆናችንን ልናሳውቅ እንወዳለን።

ከሰላምታ ጋር
የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

የኢትዮጵያውያን ማህበር በአውሮፓ    e-mail: admin@ethiodiaspora.net